# የታካሚ መብቶችና ኃላፊነቶች

Children's Health℠ እያንዳንዱ ወላጅ'ርህራሄ፣ አክብሮትና ምቾት በተሞላው መንገድ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብቱን ያረጋግጣል። በ Children's Health ውስጥ የሚታከም ሰው ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም ሕጋዊ ወኪል በመሆንዎ፣ መብቶችዎንና ከመብቶችዎ ጋር የተያያዙ የሆስፒታሉን ፖሊሲዎች በተመለከተ መረጃ የማግኘት መብት አልዎት።

## ወላጆች በመሆናችሁ የሚከተሉት መብቶች አሏችሁ፡

- የልጅዎን የጤና እንክብካቤ በተመለከተ በሚወሰዱ ውሳኔዎች ላይ በንቃት *መሳተፍ*።
- ልጅዎን የሚንከባከቡትን ሃኪሞች፣ ነርሶችና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች ስም *ማወቅ* ።
- ሕጉ እስከሚፈቅደው ድረስ፣ የልጅዎን ሕክምና በተመለከተ የተደረጉ የመልዕክት ልውውጦችና መዛግብት በሙሉ ግላዊነትና ሚስጥራዊነትን *ማስጠበቅ* ።
- ስለልጅዎ ሕመም፣ ሕክምና ወይም የማገገም ዕድል በተመለከተ እርስዎ በሚረዱት ቃላት ወይም ቋንቋ ከሃኪሙ *መረጃ የማግኘት* ።
- ሊሰጥ የታሰበን ማንኛውም ሕክምና በተመለከተ የፈቃድ ስምምነትዎን ለመስጠት ወይም ላለመስጠት የሚያስፈልግዎትን በቂ መረጃ *ማግኘት* ።
- የልጅዎን የጤና እንክብካቤ በተመለከተ ከልጅዎ ዶክተር ጋር በመመካከር *ውሳኔመወሰን*። በዚህም ውስጥ የሚካተተው በሕጉ በተፈቀደው መሰረት የልጅዎን የሕክምና እንክብካቤ የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብትና ያለመቀበሉ ስለሚያስከትለው ውጤት መረጃ ማግኘት ነው።
- በሕጉ በሚፈቀደው መሰረት ለልጅዎ የቅድሚያ መመሪያ (ለምሳሌ "የቁም ኑዛዜ") *መሙላት* እና የልጅዎ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎችም ይህን መመሪያ እንዲከተሉ መጠበቅ።
- የልጅዎ ሕመም በአግባቡ እንደሚስተናገድ *መጠበቅ* ።
- የልጅዎን እንክብካቤ በተመለከተ በስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ላይ *መሳተፍ* ።
- ጥሪ ለማድረግና ለመቀበልና እንዲሁም የሕክምና ምክንያቶችን የተመለከቱ ማናቸውም ገደቦች ላይ ከእርስዎ ጋር መወያየት እንደሚቻል ለማወቅ ስልክ *መጠቀም* ።
- የልጅዎን የሕክምና መዛግብት ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ *ማየት* ።
- የቤተሰብዎ አባል ወይም የመረጡት ወኪልዎ እና የልጅዎ ሃኪም ልጅዎ ወደ ሆስፒታል መግባቱን እንዲያውቁ *ማድረግ* ።
- ልጅዎ የሚሞት ከሆነም ምቾትና ክብር በተሞላው መንገድ እንዲስተናገድ *ማድረግ* ። በዚህም ውስጥ የሚካተቱት የልጅዎነ ሕመም መቆጣጠር፣ ለሕክምና ምላሽ የሚሰጡ ምልክቶችን ማከምና የእርስዎን፣ የልጅዎንና የቤተሰብዎን ባህላዊ፣ መንፈሳዊና የሃዘን ስሜቶች ማወቅ ናቸው።
- ከማንኛውም ሰው ትንኮሳ ወይም ጥቃት ነጻ የሆነ እንክብካቤ *ማግኘት* ።
- ልጅዎ ለሕክምና አስፈላጊ ካልሆኑ አካላዊ ወይም የጤና ገደቦች ነጻ እንዲሆን *ማድረግ* ።
- ሁኔታው አጣዳፊ ካልሆነ በስተቀር፣ ልጅዎ ለባህርይ አስተዳደር ከመገደብ ወይም ከመገለል ነጻ እንዲሆን *ማድረግ* ።
- ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንክብካቤ *ማግኘት* ።
- በዘር፣ በቀለም፣ በብሄራዊ ማንነት፣ በፆታ፣ በጾታዊ ዝንባሌ ፣ በአካል ጉዳት፣ ወይም በባህላዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወይም በትምህርት ደረጃ ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግ በትህትና እና በአክብሮት *መስተናገድ*።
- የልጅዎን እንክብካቤና ሕክምና የሚመለከት ማንኛውም የምርምር ፕሮጀክት ውስጥ ለመሳተፍ *ፈቃደኛ አለመሆን* ።
- ቅሬታ ለማቅረብና ግብረ መልስ ለማግኘት *ነጻ መሆን*።
- አስፈላጊ ሲሆን፣ የጥበቃ አገልግሎት ሰጪዎችን ለማነጋገር እገዛ *ማግኘት*

## ታካሚ በመሆናችሁ፣ የሚከተሉት መብቶች አሏችሁ፡

- እዚህ የመጡበትን ምክንያት ይረዱ ዘንድ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ **ማግኘት** ።
- ምን እንደሚካሄድና ምን ዓይነት ስሜት እንደሚኖረው **መረጃ ማግኘት** ።
- ሕክምናውነ በተመለከተ ለሚያቀርቧቸው ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች እርስዎ ሊረዱት የሚችሉትን መልስ **ማግኘት** ።
- ስለ ሕክምናዎ ምን እንደሚያስቡና ምን እንደሚሰማዎት፣ እንደዚሁም ምን ሊደረግልዎት እንደታቀደ ለሁሉም ሰው **መንገር** ።
- እርስዎ ሕመም ላይ በሚሆኑበት ጊዜ የሚንከባከቡዎተ ሰዎች እርስዎን አዳምጠው የተሻለ ስሜት እንዲሰማዎ እንደሚያግዙዎት **ማወቅ** ።
- የመጫወቻ እና የመማሪያ ጊዜ **ማግኘት** ።
- ሰውነትዎን መነካካት ያለባቸው ባለሙያዎች በትክክል ምን እንደሚያደርጉና በጥንቃቄና ግላዊ መብትን በጠበቀ መንገድ እንደሚያደርጉት **መረጃ ማግኘት** ።
- በተቻለ መጠን እርስዎ እስከፈለጉ ድረስ ቤተሰብዎ አብሮዎት እንዲሆን **ማድረግ** ።
- ወደ ቤትዎ በሚሄዱበተ ጊዜ ራስዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለማወቅ እገዛ **ማግኘት** ።
- በእርስዎ ላይ በሆነው ነገር **መናደድ** ፣ ማልቀስ ወይም ያልተመቸዎትን ነገር መናገር።
- በወላጆችዎ በተፈቀደላቸው ጠያቂዎችዎ **መጎብኘት** ። ወላጅ ይህን ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ ማስቀረት ወይም መሻረ ይችላሉ።

## ታካሚዎችና ወላጆች በመሆናችሁ፣ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሏችሁ፡

- ሕክምናውን በተመለከተ ያልገባችሁ ነገር ካለ ጥያቄዎችን **የመጠየቅ** ።
- የታካሚውን ጤና በተመለከተ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ **የመስጠት** ።
- እርስዎና የጤና እንክብካቤ ቡድንዎ በጋራ የተስማማችሁበትን **የሕክምና ዕቅድ የመከተል** ።
- ሕመምና የሕመም አስተዳደርን በተመለከተ ምን እንደሚጠብቁ ከዶክተርዎ ጋር **መነጋገር** ።
- ለሌሎች ታካሚዎች **ርህራሄ ማሳየት** ።
- የሆስፒታሉን ደንቦችና መመሪያዎች **መከተል** ።
- እንክብካቤው የሚያስከትላቸውን ታሳቢ ስጋቶችና በታካሚው የጤና ሁኔታ ውስጥ ያልተጠበቁ ለውጦችን **ሪፖርት ማድረግ** ።

## ከሚከተሉት አካላት ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታለን፡

- የልጅዎ ነርስ ወይም ሃኪም።
- የነርስ ሃላፊ ወይም ዳይሬክተር።
- የእንገዶች ግንኙነት ተወካይ በስልክ ቁጥር 214-456-2273።
- የነርሶች ሱፐርቫይዘር (ምሽት ወይም ቅዳሜና እሁድ፣ ይደውሉ 214-456-7000)።

እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ የታካሚነት መብቶችዎ አልተከበሩም ብላችሁ ካሰባችሁ፣ ለ Children's Health የቅሬታ ፈቺ ኮሚቴ ቅሬታችሁን አቅርባችሁ ምላሽ ማግኘት ትችላላችሁ ወይም ከታች ከተዘረዘሩት መ/ቤቶች ለአንዱ ቅሬታ ማቅረብ ትችላላችሁ።

ያቀረባችሁት ጥያቄ በ Children's Health መፍትሄ አልተሰጠውም የሚል ሐሳብ ካላችሁ፣ የሚከተለውን አካል ማነጋገር ትችላላችሁ፡

**The Joint Commission Office of Quality and Patient Safety (የጥራትና የታካሚ ደህንነት የጋራ ኮሚሽን ጽ/ቤት)**
One Renaissance Boulevard
Oakbrook Terrace, Illinois 60181
patientsafetyreport@jointcommission.org

**Health Facility Compliance Group**
(MC 1979)
Texas Department of State Health Services
P.O. Box 149347
Austin, Texas 78714
**hfc.complaints@dshs.state.tx.us**
1-888-973-0022 Complaint Hotline
1-512-834-6653 Fax